በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

የተሰጠ መግለጫ

ነሐሴ 12 ቀን 2005ዓ.ም

# ወቅታዊ ጥሪ ለመምህራን

በሀገራችን ቁልፍ  የትምህርት ችግር ተደርጎ እየተነገረ ያለው የትምህርት ጥራት ማሽቆልቆልና በአሁኑ ጊዜ የባሰ መውደቅ ነው። የትምህርትን ጥራት ለማምጣት የሚያስችሉ ሌሎች ተጨቃሽ ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው የመምህሩ  ጥራትና ብቃት ለትምህርቱ ጥራት ወሳኝ መፍትሔ ነው። መምህራን ጥራትና ብቃት እንዲኖራቸው ካስፈለገ ደግሞ ተገቢው ስልጠና ሊሰጣቸውና ወደ ስራ ዓለም ከተሰማሩም በኋላ የረጅምና የአጭር ጊዜ የሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎች እየተዘጋጁ ከፖለቲካ ታማኝነት በፀዳ መልኩ ሊሰጥ ይገባል። ከዚህም ባሻገር ወደ ትምህርት ሴክተሩ የሚገቡ ሰልጣኞች በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት ወይም አማካይ ውጤት ያስመዘገቡ መሆንና የመመልመያ መስፈርቱም ከአድልኦ የጸዳ መሆን ይገባዋል። ሆኖም ግን የመምህርነት ሙያ ለመኖር የሚያስችል በቂ ክፍያ የሌለው በመሆኑ በትምህርታቸው የተሻለ ውጤት ያላቸው ተማሪዎች የመምህርነትን ሙያ ተመራጭ  የሥራ መስክ አድርገው አይመለከቱም ። በመሆኑም በትምህርታቸው ዝቅተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ለመምህርነት ሙያ ይመለመላሉ። እነርሱም ቢሆኑ ሌላ ሥራ ማፈላለጊያ እንጂ በሙያው የመቆየት ፍላጎት የላቸውም ። ምንም ሌላ አማራጭ ያጡ ሆነው ካልተገኙ በስተቀር ። ይልቁንም እራሳቸውን አሻሽለው ይሁን ሳያሻሽሉ ባላቸው ፖለቲካዊ ታማኝነት ብቻ እውቀትና ችሎታቸው በማይመጥናቸው ቦታ እየተሾሙና እየተመደቡ የተሻለ ክፍያ ወደሚያገኙበት ወደሌሎች ሙያዎች መሄድን የሚመርጡ ናቸው።

ይኸ በእንዲህ እንዳለ በአሁኑ ጊዜ ት/ቤቶች ሙሉ በሙሉ የገዢው አብዮታዊ ዴሞክራሲ የፕሮፖጋንዳ ማእከል ሆነው እያገለገሉ መገኘታቸው መምህሩ  አካዳማዊ ነጻነቱን እንዲያጣና ሙያውን እንዲጠላ አድርጎታል ። ፖለቲካው ሙሉ አካሉን በት/ቤቶች ማስገባቱና የት/ቤቶች አመራርና አስተዳደር በካድሬ ሹመኞች መዳፍ ውስጥ መውደቁ ለትምህርት ጥራት መውደቅ በምክንያትነት ሊጠቀስ የሚችል ነው ። ፖለቲካው በመምህሩ ላይ ባሳረፈው ጫናና በሚከፈለው አነስተኛ ደመወዝ ኑሮውን በአግባቡ ለመምራትና ችግርን ለመቋቋም ባለመቻሉ ድሬዳዋ ተካሄዶ በነበረው የትምህርት ሚኒስትር የትምህርት አመራርና አስተዳደር ጉባኤ ላይ የወያኔ ከንድ ሆኖ ሲያገለግል የነበረውና አሁንም በማገልገል ላይ የሚገኘው ተለጣፊ መምህራን ማህበር በስብሰባው ላይ ተሳታፊ ሰለነበረ የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄን ለሰብሰባው ተሳታፊዎች ለይስሙላ አቀረበ። ለወያኔ/ኢህአዴግ መንግሥት እንዲቀርብም ጠየቀ ። ወያኔና ተለጣፊው ማህበሩ መምህራንን ለማጥቃት በጋራ የሚሠሩ በመሆናቸው ቀረበ ለተባለው የደመወዝ ጭማሪ መልስ የሚሰጠው ጠፋ ። መምህራን ግን የደመወዝ ጭማሪው አስፈላጊነት ላይ አምነው እንቅስቃሴ ማድረግ ጀመሩ። በተመከሮ እንዳየነው መምህር የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄ የሚያነሳው ከነቤተሰቡ ተርቦና ታርዞ ኑሮውን ጨርሶ ለመቋቋም ሲሳነው ነው ። መምህር ላቡን አንጠፍጥፎ እውቀቱን አፍስሶ ጉልበቱን አሟጦ እንደ እርጉዝ ሴት ቀን ቆጥሮ ከሚያገኘው ንጹሕ የወር ደመወዙ በስተቀር ሌላ የጎንዮሽ ገቢ የለውም ። ከዚህም በተጨማሪ ጊዜ የሰጣቸው ካድሬዎች በየዓመቱ የትምህርት መጀመሪያና ማጠናቀቂያ ወቅት ግምገማ ፣ሂስና ግለሂስ በሚል ማደንዘዣ በቁስሉ ላይ ጨው ይነሰንሱበታል። የመምህሩ የደመወዝ ይጨመርልኝ ጥያቄ እንደሙሰኛ ካድሬዎች የቅንጦት ኑሮ አምሮት ወይም ገንዘብ በባንክ የማስቀመጥ ሱስ ይዞት ወይም ሰማይ ጠቀስ ሕንፃ ሊገነባበት አይደለም ። እየተከፈለ ያለው ወርሀዊ ደመወዝ በዝቅተኛ ደረጃም ሊያኖረው ስላልቻለ ፤ ስለተራበና ስለታረዘ  ነው እንጂ። በመሆኑም ከመምህሩ የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄ ጋር በተያያዘ በየካቲት ወር 2004 ዓ.ም መንግሥት ለመምህራን አደረኩት ባለው የደመወዝ ጭማሪ ቅር በመሰኘት በመጋቢት ወር 2004 ዓ.ም መምህራን በአንዳንድ ት/ቤቶች በአዲስ አበባና በጎንደር የሥራ ማቆም አድማ ማድረጋቸውና ሌሎችም የተደረገው የደመወዝ ጭማሪ ከወቅቱ የኑሮ ውድነት አኳያ ሲታይ እዚህ ግባ የማይባል መምህራንን ያዋረደና የሙያውን ክብር ዝቅ ያደረገ ሆኗል። ይህንንም የደመወዝ ጭማሪ ተከትሎ ቤት አከራዮች በመምህራን ተከራዮች ላይ በተለይ የኪራይ ጭማሪ ጭነውባቸዋል። ይህም ቀድሞውኑ እየናረ ከሄደው የመሰረታዊ ምርቶች ዋጋ ጋር ተደምሮ በመምህራን ኑሮ ላይ የከፋ ገጽታ በመፍጠሩ መምህራን ተቃውሟቸውን አሳሙ ።

P.O.Box 16632 Saint Paul, MN 55116 • Tel.: 403-402-0334 • Email: eta1941@yahoo.com

*በዚህ ወሳኝ ወቅት ለወያኔ/ኢህአዴግ መንግሥስት የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግ ጥያቄ አቀረብኩ ያለው ተለጣፊ ማህበር መሪዎች ከመንግሥት ጎን በመቆም የመምህራንን የመብት ጥያቄ ትግል ለማኮላሸት በቴሌቪዥን፣ በሬዲዮ ጣቢያና በተለያዩ የስብሰባ መድረኮች በመቅረብ ጸረ- መምህርነቱን በተግባር አሳይተዋል። ከመንግሥት ጋር በመሆን መምህራንን አጥቅተዋል። ይህንንም ተከትሎ አንዳንድ መምህራን (ከአዲስ አበባ ስድስት እንዲሁም ከጎንደር ስድስት በጠቅላላው 12 መምህራን) ከሥራ መባረራቸውና ከእነዚህም ውስጥ የተወሰኑት ወደ ሥራቸው ሲመለሱ ፣ ሶስት መምህራን ከአዲስ አበባ እስካሁን ወደ ሥራቸው አልተመለሱም። ከቤተሰቦቻቸው ጋር ችግር ውስጥ ናቸው። ኢትዮጵያዉያን እነዚህን ወገኖች ሊረዱ ይገባቸዋል። በጊዜው የወያኔ መንግሥትና የመንግሥት ቁንጮ የነበሩት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በሚያዚያ ወር 2004ዓ.ም በቴሌቪዢን መስኮት ቀርበው "መምህራን የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄ አልጠየቁም ፤ ያልተጠየቅነውን አላስተናገድንም ፤ ማህበሩ በድሬዳዋ የጠየቀው የደመወዝ እስኬል ማስተካከያ ነው ። ፍትሀዊ ስላልነበር ያስተካከልነው እስኬሉን ነው ፤ ይህም የደመወዝ እስኬል ማስተካከያ ከተደረገ በኋላ መምህሩ በየዓመቱ ወደ ጎን የደመወዝ እርከን ጭማሪ ይደረግለታል ፤ መምህሩም ተጠቃሚ የሚሆነው ያን ጊዜ ነው።" በማለት መግለጫ ሰጥተው ነበር ። የመምህራንን የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄን ለማስተናገድ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ። ጥያቄያቸውንም አጣጣሉት ። በእሳቸው ሳምባ በሚተነፍሰው ፓርላማም የደመወዝ ጥያቄ ያነሱትን፣ ለመብታቸው የሚታገሉትንና በመምህርነት ሙያም አንቱ የተባሉትን መምህራንን የሙያ ብቃትና የስነምግባር ጉድለት ያላባቸው ናቸው በማለት ተሳደቡ ። ከዚያም ብዙ በደል በማህበሩና በአባላቱ ላይ እንዲፈጸም መመሪያ ወጥቶ ተግባራዊ ተደርጓል ። የማህበሩ አመራር ከት/ቤት መሰረታዊ ጀምሮ እስከ አገር አቀፍ ድረስ በካድሬ መምህራን እጅ ወድቋል። የማህበሩ ሀብትና ንብረት እየተዘረፈ ይገኛል። የእስኬል ማስካከያዉን በሚመለከት ግን የትምህርት ሚኒስትር ተግባራዊ እንዲደረግ በቁጥር 13/1-10012/8297/35 በቀን 15/09/2004 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የመምህራን ፣ ር/መምህራን፣ ም/ር/መምህራንና ሱፐር ቫይዘሮች የደመወዝ ማስተካከያ ማስፈጸሚያ መመሪያ ለዞንና ወረዳዎች ልኳል። ሆኖም ግን ይህ የመምህራን ፣ የር/መምህራን ፣ የም/ር/መምህራንና የሱፐርቫይዘሮች የደመወዝ እስኬል ማሻሻያ ተግባር ላይ እንዲውል ከተወሰነበት መጋቢት 1 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ካንድ ዓመት በላይ አስቆጥሯል። የእርከን ጭማሪው የሚደረገው በየዓመቱ በመሆኑ ራሱ መንግስት ባወጣው መመሪያና ደንብ መሰረት ከመጋቢት 1 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ መምህራን የእርከን ጭማሪ መግኘት ይገባቸው ነበር ። ነገር ግን ተፈጻሚ አልሆነም። ይህም በመሆኑ በሰኔ ወር 2005ዓ.ም በተደረገው የ2005 ዓ.ም የት/ቤቶች እቅድ አፈጻጸም ግምገማና የሂስና ግለሂስ መድረክ በአንዳንድ ት/ቤቶች ከተነሱት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱ ይኸው በየዓመቱ የእርከን ጭማሪ እንደሚደረግ የተላለፈውን መመሪያና ደንብን የሚመለከት ነበረ። በወቅቱ በዚሁ የእርከን ጭማሪ ዙሪያ ለተነሳው ጥያቄ የበላይ አካል ተጠይቆ ምላሽ የሚሰጥበት መሆኑን ከመድረክ መሪዎች አንደበት ተደምጧል። ለዚህም ብዙ መረጃዎች አሉ። ከትምህርት ሚኒስትር የተላለፈውን መመሪያ ተግባራዊ ማድረግ የዞኖች፣ የወረዳና የት/ቤቶች ትምህርት አመራርና አስተዳደር ዘርፍ ኃላፊነት ነው ። እንደገና የበላይ አካል የሚጠየቅበት ምክንያት የለም ። መምህራንን ለመጉዳት የሚፈጸም ሌላ ሰውር ተንኮል እስከሌለ ድረስ።*

*ከትምህርት ሚኒስትር የተላከውን የደመወዝ ስኬል መመሪያ መምህራን እንዲያውቁት ደረጃውን ( ከI - XIV)፣ መነሻውን ደመወዝ ለሁሉም ደረጃዎች፣ ለሁሉም ደረጃዎች ከ1-9 የእርከን ደመወዝ ጭማሪና ለሁሉም ደረጃዎች የጣሪያ ደመወዝ ልክ የሚያሳያውን ሰንጠረዥ ከዚህ መግለጫ ጋር አባሪ የተደረገ ስለሆነ ይመልከቱ።*

*በመስከረም ወር 2006 ዓ.ም የትምህርት ሳምንት ተብሎ በሚደረገው ሰብሰባ ላይ ይህን የእርከን ጭማሪ ጉዳይ ተዳፍኖ እንዳይቀር ምላሽ እንዲያገኝ ለማድረግ ሁሉም መምህር ጥያቄውን አጠናክሮ እንዲያነሳ፣ ይህ እንኳን ተግባራዊ ቢሆን የሚከፈለው ገንዘብ አሁን አገሪቱ ባለው የኑሮ ወድነትና የምርት ኢቃዎች ዋጋ መጨመር ጋር ሲነፃፃር የመምህሩንና ቤተሰቡን ኑሮ የማይለውጥ ስለሆነ የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግ ጥያቄውን አሁንም እንዲያነሱና እንዲታገሉ ፣ ወያኔ ማህበራቸው ውስጥ ያደረገውን ጣልቃገብነት ለማስወገድ በስልትና በጥንቃቄ እንዲደራጁ፣በአጠቃለይ መብታቸውንና ጥቅማቸውን ለማስከበር፣ ጥራት ያለው ትምህርት ለሕዝብ ልጆች እንዲሰጥ ፣በአገሪቱ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሰፍን ለማድረግ መምህራን የበኩላቸውን ግዴታ እንዲወጡ በሰደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ ጥሪውን ያስተላልፋል።*

*የመምህራን መብት በትግላችን ይከበራል!!*
*መብታችንን ለማስከበር ሕብረት ወሳኝ ነው!!*

<u>ሰንጠረዥ-2 የመምህራን፣የርዕሰ መምህራን እና የሱፐርቫይዘሮች የደመወዝ ስኬል /ነሀሴ 2003 ዓ/ም/</u>

| ደረጃ | የትም/ቤቱ ደረጃና የስራ መደቦች | | | | የመነሻ ደመወዝ | የእርከን ደመወዞች | | | | | | | | | ጣሪያ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የአፀዱ ህፃናት | ከ1-8 | 9-10 | [illegible] | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | |
| I | ጀ/መምህር | | | | 908 | 957 | 1006 | 1059 | 1114 | 1172 | 1233 | 1295 | 1359 | 1427 | 1499 |
| II | መስ/መምህር | | | | 1059 | 1114 | 1172 | 1233 | 1295 | 1359 | 1427 | 1499 | 1571 | 1644 | 1719 |
| III | መምህር | ጀማሪ መምህር | | | 1233 | 1295 | 1359 | 1427 | 1499 | 1571 | 1644 | 1719 | 1798 | 1881 | 1968 |
| IV | ከ/መምህር | መስ/መምህር | | | 1427 | 1499 | 1571 | 1644 | 1719 | 1798 | 1881 | 1968 | 2058 | 2151 | 2249 |
| V | ተባባሪ መሪ | መምህር | ጀማሪ መምህር | | 1644 | 1719 | 1798 | 1881 | 1968 | 2058 | 2151 | 2249 | 2351 | 2458 | 2570 |
| VI | መሪ መምህር | ከፍተኛ መምህር | መስ/መምህር | | 1881 | 1968 | 2058 | 2151 | 2249 | 2351 | 2458 | 2570 | 2686 | 2807 | 2934 |
| VII | ከፍተኛ መሪ መምህር | ተባባሪ መሪ መምህር ጀማሪ ም/ር/መምህር | መምህር | [illegible] | 2151 | 2249 | 2351 | 2458 | 2570 | 2686 | 2807 | 2934 | 3066 | 3204 | 3348 |
| VIII | | መሪ መምህር ም/ርዕሰ መምህር ተባባሪ ሱፐርቫይዘር | ከፍተኛ መምህር | መስ/መምህር | 2458 | 2570 | 2686 | 2807 | 2934 | 3066 | 3204 | 3348 | 3499 | 3656 | 3817 |
| IX | | ከፍተኛ መሪ መምህር ከ/ም/ርዕሰ መምህር ጀማሪ ርዕሰ መምህር ሱፐርቫይዘር | ተባባሪ መሪ መምህር ጀማሪ ም/ር/መምህር | መምህር ጀማሪ ም/ር/መምህር | 2807 | 2934 | 3066 | 3204 | 3348 | 3499 | 3656 | 3817 | 3985 | 4160 | 4343 |
| X | | መሪ ም/ርዕሰ መምህር ርዕሰ መምህር ከፍተኛ ሱፐርቫይዘር | መሪ መምህር ም/ርዕሰ መምህር | ከፍተኛ መምህር ም/ርዕሰ መምህር | 3204 | 3348 | 3499 | 3656 | 3817 | 3985 | 4160 | 4343 | 4535 | 4734 | 4933 |
| XI | | ከፍተኛ ርዕሰ መምህር መሪ ሱፐርቫይዘር | ከፍተኛ መሪ መምህር ከ/ም/ርዕሰ መምህር ጀማሪ ርዕሰ መምህር ተባባሪ ሱፐርቫይዘር | ተባባሪ መምህር ከ/ም/ርዕሰ መምህር ጀማሪ ርዕሰ መምህር ተባባሪ ሱፐርቫይዘር | 3656 | 3817 | 3985 | 4160 | 4343 | 4535 | 4734 | 4933 | 5135 | 5340 | 5554 |
| XII | | መሪ ርዕሰ መምህር | መሪ ም/ርዕሰ መምህር ርዕሰ መምህር ሱፐርቫይዘር | መሪ መምህር መሪ ም/ርዕሰ መምህር ርዕሰ መምህር ሱፐርቫይዘር | 4160 | 4343 | 4535 | 4734 | 4933 | 5135 | 5340 | 5554 | 5776 | 5998 | 6225 |
| XIII | | | ከፍተኛ ርዕሰ መምህር ከፍተኛ ሱፐርቫይዘር | ከፍተኛ ርዕሰ መምህር ከፍተኛ ሱፐርቫይዘር | 4734 | 4933 | 5135 | 5340 | 5554 | 5776 | 5998 | 6225 | 6460 | 6704 | 6958 |
| XIV | | | መሪ ርዕሰ መምህር መሪ ሱፐርቫይዘር | መሪ ርዕሰ መምህር መሪ ሱፐርቫይዘር | 5340 | 5554 | 5776 | 5998 | 6225 | 6460 | 6704 | 6958 | 7218 | 7488 | 7768 |